# *<u>ወያኔዎች ባማራ ህዝብ ላይ በከንቱ የዘሩት የዘር ጥላቻና ለዘመናት የፈጸሙት በደል በትንሹ ሲገለጥ ።</u>*

## *እኔ ባይኔ ያየሁትንና በጆሮየ የሰማሁትን ብቻ ለመግለጽ እወዳለሁ፥*

*በኢትዮጵያ  የዘመን አቆጣጠር  በ1975 ዓ/ም  ወይም በፈረንጆች የዘመን አቆጣጠር በ 1983 ዓ/ም ከኢትዮጵያ ወደ ሱዳን ተሰድጀ ገባሁና ለጊዘው መኖርያዬን በገዳሪፍ ከተማ አደርኩ። በከተማውም ለሁለት አመት ያክል ኑሪያለሁ። ከዛም ከተለያዩ ከተማዎች በመዘዋወር ለ 12 ዓመታት ሱዳን ውስጥ ኑሪያለሁ። በዚሁ በነበርኩበት ጊዜ አማረኛ የሚናገር ስደተኛ በፖለቲካ ድርጅት ካልታቀፈ በቀር ደርግ የሚል ስም እየተሰጠው ወዳልታወቀ ቦታ እየተወሰደ የሚጠፋው በጣም ብዙ ነበር።*

*ትግረኛ ተናጋሪ መሆን ግን እንደ ሱዳን ዜጋ የሚቆጠርበት ሁኔታ ይታይ ነበር። በተለይም የሻብያ እና የወያኔ ድርጅቶች አባል መሆን በሱዳን መንግስትም ሆነ በሱዳን ወታደራዊ አዛዦች እንደፈለጉ ለመንቀሳቀስ ሙሉ መብት ይሰጣቸው ነበረ። ድንገት እንኳ በሆነ ነገር ተይዘው ቢታሰሩ በ24 ሰዓት ውስጥ በትግረኛ ተናጋሪነታቸው ምክንያት ይለቀቁ ነበር።*

*በዛን ጊዜ ለትግራይ ሕዝብ በወያኔ በኩል የሚነገረው ነገርና የሚሰጠው ቅስቀሳ በጣም የሚያሳዝን ነበር። ይህም ለትግራይ ህዝብ ድህነት፣ኃላ ቀርነት፤ማህይምነት ፣ወዘተ ተጠያቂው የአማራ ህዝብ ተደርጎ ይነገራቸው ነበር። ከአማራ ሕዝብ ቀጥሎ የመጭቆኛ መሳሪያ እንደነበረ ተደርጎ የሚነገራቸው አማረኛ ቋንቋ ነበር። በሁለተኛ ደረጃ ተጠያቂ የኦርቶዶክስ እምነት ነበር። የትግራይ ህዝብ አብዛኛዎች የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ናቸው። ግን ልክ አማራውን ጠላት አድርገው እንዳስቀመጡት ሁሉ የኦርቶዶክስን እምነትም በጠላትነት ፈርጀው ብዙ የትግራይን ቄሶችን ሳይቀር እንደበደሏቸውና እንደ ገድሏቸው እዛው በስደት ያገኘናቸው የትግራይ ተወላጆች በምሬትና በሃዘን ነግረውኛል።*

*በተለይ አማራ ጠላታችን አይደለም የሚሉና የኦርቶዶክስን እምነት የሚያከብሩና የኢትዮጵያን የሶስት ሺህ ዘመን የሚቀበሉ የትግራይ ተወላጆች ተደብደበዋል፣ተወርሰዋል፣ተገድለዋል። ከዚህም ጋር በተያያዘ በተለይም በኢ.ድ.ዩ አባላትና ደጋፊዎች ላይ ብዙ በደል ተፈጽሟል። በዚህም የተነሳ ሱዳን አገር ውስጥ እንጉልጃ ከሚባል የኢትዮጵያ ስደተኞች ሰፈር የትግራይ ወጣት ወያኔዎች እና የትግራይ ኢ.ድ.ዩ የነበሩ አባቶች በሚገርም ሁኔታ ተገዳድለዋል። በአንድ ቀን ከ30 ሰው በላይ ከግራ ቀኙ ተገድሎ ውሏል።*

*እንግዲህ ከላይ እንደተገለጸው ወያኔዎች አማራ የተግራይ ሕዝብ ጠላት ነው በማለት ከፍተኛ የውሸት ታሪክ እየፈጥሩ በተለይ ለአዲሱ ትውልድ የጥላቻ ቅስቀሳ ያካሂዱ ነበር። ኢትዮጵያም የ3000 ዓመት ታሪክ ያላት አገር ሳትሆን የ 100 ዓመት ታሪክ ያላት አገርናት እያሉ ወጣቱን የትግራይ ትውልድ በኢትዮጵያ አንድነት ላይና ባማራ ሕዝብ ላይ የተሳሳተ ታሪክ በማስተማር ጥላቻና ጭካኔን ይዞ እንዲወጣ ይቀሰቅሱ ነበር።*

*እንዲህም እያሉ በበርሃ ለሚኣሳድጓቸው ወጣቶች ያስተምሩ ነበር፥ ሃደ ተጋዳላይ አርባአተ አማሃራ እንደሀር ቀትሎ ከሊ ተጋዳላይ ድማ ከሊ አርባተ አማህራ እንደሀር ቀትሎ ከድመር ከንደይ አማህራ ሞይቶ ብለው በሂሳብ ትምህርት ያስተምሩ ነበር። ወደ አማረኛ ሲተረጎም አንድ ተጋዳይ አራት  አማራ ቢገድል ሌላኛው ተጋዳይ ደግሞ ሌላ አራት አማራ ቢገድል ሲደመር ስንት አማራ ሙቷል ወይም ተገድሏል ማለት*

*ነው። ይህ የትምህርት ስሌት የትግርኛ የልጆች ማስተማሪያ ከሁለተኛ እስከ ሶስትስኛ ክፍል በሚኣስተምሩበት የሂሳብ መጽሃፋቸው ላይ ተጽፎ ኣይተነዋል። እግዚአብሄር ያሳያችሁ እንደዚህ በዚህ ሁኔታ ተምሮና ተነግሮት ያደገ ልጅች ምን ኣይነት ስነ ልቦናና ስነ ኣምዕሮ እንደሚኖራቸው ገምቱ። ዛሬ እንደዛ ተምረው ያደጉት ልጆች ናቸው ያሁኖቹ የጦር መሪዎች፣ካድሬዎች፣ደህንነቶች ለዛም ነው እንዲህ በየከተማው ያማራን ልጅና ሌላውንም በጭካኔ እየፈጁ የሚገኙት።*

*ለዚህ የጥላቻ ድርጊታቸው ኣንድ ተጭማሪ ማስርጃ ላስቀምጥ። በ1985 በፈርንጆቹ የዘመን አቆጣጠር ወይም በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር በ1976ና 1977 ዓ/ም ይመስላኛል ትግራይ ክፍለሃገር ድርቅ ሁኖ የትግራይን ህዝብ ገሚሱን ደርግ ወደ ማህል ኣገር ሲያጓጉዘው ገሚሱን ደግሞ ወያኔዎች ወደ ሱዳን በተለይ የትግራይን ገበሬ ወደ ሱዳን ኣገር ኣጉዘውት ነበረ። ይህን ሰደተኛ የትግራይ ገበሬ ሱዳን ኣገር ውስጥ በገዳሪፍና በመደኔ መካከል ጀበልፋው በሚባል ቦታ በ4 የሰፈራ ጣቢያ ኣሰፈሩት ይህነን የትግራይን ሰደተኛ ህዝብ ለመርዳት ኣይ. ኣር. ኤስ የሚባል የኣሜሪካን የርዳታ ድርጅት ገብቶ ለዚህ ህዝብ ኣግልግሎት የሚሰጡ በርካታ በገዳሪፍና በኣካባቢው የተገኙ ኢትዮጵያኖችን በብዛት ቀጥሮ ነበር።*

*በዚህ ጊዜ እንደግል ንብረት በወያኔ ተይዞ የነበርው የትግራይ ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ለመገናኘትና ለመወያየት እድል ፈጥሮለት ነበር። በዚህም ኣጋጣሚ ኣማራ ጠላቱ ኣለመሆኑን እየተረዳ ሲመጣ ጎረምሳ ጎረምሳ የሆነው የትግራይ ሰደተኛ ከነበረበት የስደተኛ ጣቢያ እየከዳ ማምለጥ ጀመረ ይህ ሁኔታ የወያኔን የወደፊት የታጋይ ሃይል ሚቀንስባቸው ሁኖ ሲያዩት ኣንድ ኣስገራሚ ተንኮል ጠነሰሱ። ይህውም እነዚህ ለርዳታ ኣገልግሎት የተቀጠሩት ኣማራዎች ናቸው ኣማራ ደግሞ ቀንደኛ ጠላታችን ነው ስለዚህ እዚህ ያለው የትግራይ ሰደተኛ ህዝብ ባማራዎች ምንም ኣይነት እርዳታ እንዲደርግለት ኣንፈልግም በማለት ይውጡልን የሚል ጥያቄ በወያኔ መሪዎች በህዝቡ ስም ጥያቄ ኣቀረቡ።*

*ኣይ. ኣር .ኤስ የተባለው የኣሜሪካን የርዳታ ድርጅት ህዝቡን እንዴት እንርዳው? ብሎ ሲጠይቅ ወያኔዎች የሰው ሃይል እኛው እራሳችን እናቀርባለን ሲሉ እነ ተወልደ የወያኔ ሰዎች መልስ ሰጡ።በዚህ ጊዜ ከተቀጠሩት ሰራተኞች ውስጥ የወያኔ ኣባል ያልሆኑ የትግራይና የጎንደር ተዎላጆች ሰደተኛው የትግራይ ህዝብ ይህነን ኣማራ ይውጣልኝ ጥያቄ ኣላቀረበም ።ሊኣቀርብም ኣይፈልግም ይህነን ያቀነባበሩት ወያኔዎች ናቸው ብለው በድፍረት ለኣይ ኣር ኤስ መሪዎች የተናገሩ ሰዎች ነበሩ።*

*ወያኔዎችም እነዚህን የመከራከሪያ ሃሳብ ያቀረቡ ግለሰቦችን በለሌት ከመኖርያ ቤታቸው ድረስ በመሄድ በዱላ ደበደቧቸው። የኣሜሪካው የርዳታ ድርጅትም ይህነን ድርጊት ሲመለከት እኛ እነዚህን ሰራተኞች የቀጠርነላችሁ ለናንተ እገልግሎቶ ሊሰጡ ነው ካልፈለጋችሁ እናሰናብታለን በሰው ህይወት ላይ ሃላፊነት ኣንወስድም በማለት የትግራይ ተወላጅ ያልሆነውን ሰራተኛ ሁሉንም የኣገልግሎታቸውን ደሞዝ እየከፈሉ ኣሰናበቱ።*

*ከዛበኃላ ሱፍ ውሃና ወዲከውሌ በምሚባለው የኣርማጭሆና ሱዳን ወሰን እና በሌሎች ቦታዎች ላሰፈሯቸው የትግራይ ሰደተኞች ኣገልግሎት የሚሰጡ ሰራተኞች ሲቀጠሩ የትግራይ ተዎላጆች ብቻ መሆን ኣለባቸው ተብሎ ተወሰነ። ይህ ሁሉ የሚሆነው የትግራይን ህዝብ ከኣማራ ህዝብ ለመለየትና ጠላት ኣድርጎ ለማስቀጠል የተደረገ ሴራ ነበር።ነገሩ በዚህ ብቻ ኣላበቃም በሌሎችም የስደተኛ ጣቢያዎች እየገቡ ህዝቡን በማለያየት ብዙ ክፉ ስራዎችን ፈጽመዋል።ለምሳሌ ኣምራኩባ በተኣባለው የኢትዮጵያ ስደተኞች የሰፈራ ጣቢያ ከሱዳን መንግስት ጋር በመስማማትና በመተባበር እዛ ኣካባቢ የሚኖሩትን ኣማራዎች*

በተለይም የፀገዴ፣ የወልቃይት፣ የአርማጭሆንና የጭልጋ አውራጃ ተወላጆችን በሱዳን መንግስት አማካኝነት ብዙ ጀግኖችን ገድለዋል። ለምሳሌ እነ ሻለቃ አስራደ በየነ፣እነ ሻለቃ ጌታቸው ይርጋ፣እነ አቶ ጌታሁን ሃጎስ ፣እነ አቶ መኩታው አዛናው እነ መሀመር ተስፋሁን አግዴ፣እነ ሻለቃ አበጀ ፈለቀ፣እነ መምህር ሰለሞን የጎጃም ልጅ፣እነ አቶ ማርቆስ እና ሌሎችም ተገድለዋል። ሊገደሉ ሲፈለጉ ከሞት ያመለጡትም ብዙዎች ነበሩ። ታዋቂው ሻለቃ አጣናው ዋሴ ካመለጡት አንዱ ነበር። ሻለቃ አጣናው በዛን ሰዓት ከሞት ይትረፍ እንጅ ወያኔዎች ኢትዮጵያን ከተቆጣጠሩ በኃላ ሱዳኖች ሻለቃ አጣናው ዋሴን ይዘው ለወያኔዎች በማስረከብ አዲስ አበባ ውስጥ አስረው እዚያው እስር ቤት ውስጥ እንዲሞት ሁኗል። ይህ ሁሉ የሚሆነው አማራን አዳክሞ የአማራን መሬት ለመዝረፍ ሲባል የሚፈጸም የንፋግ ወያኒዎች ግፍ ነው። ሱዳኖችም ቁራሽ መሬት ይሰጣችኋል የሚል አጉል ተስፋ ስለነበራቸው ነው።

በ 1991 በፈረንጆች አቆጣጠር ደርግ ከስልጣኑ እንደ ወረደ ሱዳን ውስጥ ይኖር የነበር የትግራይ ተወላጅ የሆነ የሰዩም መስፍን አጎት የሚባል  ጥንት በሁመራ የልማት ጊዜ ሁመራ ላይ ባላሃብት የነበር ተስፋየ አዷ የሚባል ለወያኔዎችና ለትግራይ ህዝብ ምክር ሲለግስ ባስችኳይ የጸገዴ ወልቃይትንና የአርማጭሆን መሬት ያዙት ብሎ በሚስጥር ምክር መስጠቱ ተሰምቶ ብዙ ሰዎች አዝነውበት እንደነበር አስታውሳለሁ።

ተስፋየ አዷ የተባለው ግለሰብ ይህነን ሊል የቻለው የወልቃይት ጸገዴ እና የአርማጭሆ ሕዝብ የደርግን አገዛዝ አንቀበልም ብሎ በኢዲዩ ስም  እና በሌሎች ሃይሎች  ስም ተደራጅቶ ጦርነት በማድረጉ ምክንያት የሁመራ፣ የአብደራፊ፣ የመተማ ሰፋፊ ዘመናዊ የርሻ ደጅቶች በመዘጋታቸው በጦርነቱ ሰበብ ከተማዎች በመውደማቸውና ሕዝቡ አካባቢውን ለቆ ወደ ተለያየ አቅጣጫ በመሰደዱና ቦታው በመለቀቁ  ነው። የገቢያ ግርግር ለሌባ ይመቻል እንዲሉ ሆነና የደርግ ሥርዓት ሲወድቅ በብልጠት ቀድሞ በአካባቢው ገብቶ ቦታ ለመዝርፍ ወይም ለመቆጣጠር ነበር ።

ወዲያውኑ በዚህው ሰውየ ማለትም በተስፋየ አድዋ ምክር መሰረት ይመስላል ወያኔዎች የዓለም ቀይ መስቀልን በሱዳን አገር ውስጥ የሚኖረውን የኢትዮጵያ ስደተኛ ደርግ ስለወደቀ ወዳገሩ ልንመልሰው ነውና ለመልሶ ማቋቋሚያ ህዝቡ እርዳታ ያስፈልገዋል በማለት እርዳታ ጠየቁ እርዳታውንም በስደተኛው ስም አግኝተዋል። የሚያሳዝነው ነገር ግን እርዳታውን የሰጡት ለመላው የኢትዮጵያ ስደተኞች ሳይሆን ለትግራይ ተወላጅ ብቻ ነበር። እርዳታውም የተገኘው ለስደተኞች መልሶ ማቋቋሚያ ማለትም  ለሰፈራ ፣ ለውሃ ፣ለሆስቲታል፣ለት/ቤት እና ለመሳሰሉት በማለት ነበር።

ሁመራ አካባቢ የተወሰነ የሰፈራ ጣቢያ ከሰሩ በኃላ ቁጥራቸው በጣም ትንሽ የሆነ የትግራይ ተዎላጆችን ስደተኞች ከሱዳን ወደ ሁመራ መልሰው ግን ደግሞ በብዛት ከደጋው ትግራይ ሕዝብ አጉዘው የሁመራንና የወልቃይትን መሬት አሰፈሩበት።

የጸገዴ ፣የወልቃይት፣ የአርማጭሆ፣ እና ሌላው የጎንደር ሕዝብ እንዲሁም ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝም በደርግና በኢድዩ፣በኢህፓና በሌሎችም መካከል በነበረው ጦርነት ምክንያት ሱዳን አገር ውስጥ ይኖር የነበረው ስደተኛ በጣም በብዙ ሺ የሚቆጠር  ሕዝብ ነበር።ነገርግን ወያኔዎች ይህ ሁሉ ህዝብ አገሩን ግብቶ ቦታ ከመያዙ በፊት የራሳችን የሚሉትን ሕዝብ ቀድሞ በአማራው መሬት ላይ በወልቃይትናጸገዴ ፣ በሁመራ፣በአብደራፊና በመተማ  ለማስፈር ተሻሙ። በተለይ ከሱዳን የነበሩትን የትግራይ ስደተኞች በብዛት ከማስፈራቸውም በላይ  በጣም የሚገረመው ነገር ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ በትግራይ የሚገባ

ስደተኛ የያዘውን ንብረት ይዞ ያለቀርጽ በነጻ እንዲገባ ሲፈቀድለት የአማራ ክልል ሕዝብ ግን ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ከያዘው የንብረት ዋጋ በላይ ቀረጥ ከፍሎ እንዲገባ ተበየነበት።

ይህ የሆነው ሁመራ ፣አብደራፊ፣አብራሃጅራ፣ማርዘነብ፣መተማ፣ እና በሌሎችም ከተማዎች የነበሩ ዘመናዊ ገበሬ ባላሃብቶች ከደርግ ጋር በነበረው ጦርነት ምክንያት ወደ ሱዳን ሲሻገሩ መኪንዎቻቸውን ይዘው ነበር። አገር ሰላም ሲሆን ተመልሰን ይዞታችን እንኖራለን የሚል ተስፋ ስንቀው ይኖሩ ነበር። ነገር ግን ወያኔ ተስፋየ አድዋ እንደተናገረው የትግራይ ህዝብ ቀድሞ ገብቶ ባማራው ይዞታ ላይ እንዲይሰፍር ሲደረግ አማራው ግን በቀረጥ ምክንያት ተጉላልቶ እንዲዘገይ ተደረገ።

ይሁን እንጅ አንዳንድ የወልቃይትና የጸገዴ ተወላጅ ባለሃብቶች የወያኔ ተንኮል ስለተረዳቸው ንብረታችንን ሌላ ጊዜ እናስገባለን አሁን ግን በባዶ እጃችን እንግባና ሁመራ ከተማ ያለውን የከተማ ቤቶቻችን እና የጥንት የርሻ ይዞታችንን እናስከብር በማለት ወደ ሁማራ ከተማ ለመግባት ሞክረው ነበር። ነገር ግን ሁመራ ሲደርሱ ወያኔዎች ወደ ሁመራ አትግቡም ተመለሱ በማለት ከለከሏቸው። ለምን ብለው ሲጠይቁ እናንተ ኢ.ዲ.ዩ ናችሁ አሏቸው። ታዲያ እኛ ኢ.ዲ.ዩ ብንሆንም እንደናንተ ለነጻነት የታገልን ለነጻገቢያ ስርዓት የተዋደቅነ ታጋዮች ነን እኮ ሌላው ደግሞ የድርጅታችን ዋና መሪ ሉዕል ራስ መንገሻ ስዩም የሽግግሩ መንግስት አባል ሁነው አዲሳበባ እየሰሩ ይገኛሉ። እኛ ወዳገራችን ለመግባት የምንከለከለው ለምንድን ነው? ብለው ቢከራከሩም ሁመራ አምጥተው ያስፈሩትን የትግራይን አዲስ ሰፋሪ ህዝብ የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ እንዲወጣባቸው አደረጉ።

ወደ ሁመራ ለመግባት ሞክረው የነበሩት የወልቃይት፣ የጸገዴ ተዎላጆች በሁኔታው በጣም አዝነውና ተበሳጭተው  ሁመራ  ሳይገቡ ወደ ነበሩበት ሱዳን ተመለሱ። በዚህ የተነሳ ብዙዎቹ ሳይፈልጉ ወደ አውስትራሊያ እና ወደ ኒውዝ ላንድ ለመሰደድ ተገደዱ። አንዳንዶቹ የነበውራቸውን ንብረት በቅናሽ ለሱዳን ህዝብ እየሸጡ ወደ ጎንደር ከተማ እና ወደ ሌሎች ክፍላተ ሃገራት ለመሄድ ተገደዱ።

የወያኔ ተንኮል በዚህ አላበቃም። በሌሎች የጎንደር አውራጃዎች ለምሳሌ በታች አርማጭሆ ወረዳ አብደራፊ ከተማ እና በመተማ እንዲሁም በሌሎች ከተማዎች ሱዳን አገር የነበሩ የትግራይ ተወላጆችን አስቀድመው አስፈሩ ጠቃሚ ቦታዎችን ለመያዝ እንዲረዳቸው የአብደራፊና የመተማን ከንቲባዎች ጥሩ አማርኛ ተናጋሪ የሆኑ የትግራይ ተወላጆችን የጎንድር ተወላጅ በማስመሰል የየከተማዎች ከንቲባ አደረጓቸው። በነዚህ ሹመኞች አማካኝነት የትግራይን ሰፋሪ ህዝቦች ቅድሚያ ቦታ አስያዙ።

በዛ መሰርት አብደራፊ የሰፈሩት የትግራይ ተዎላጆች በኢትዮጵያ አቆጣጠር 2005 ዓ/ም ከአብደራፊ እስከ መተማ ድረስ ያለውን መሬት ወደ ትግራይ ክልል ተጠቃሎ ይከለልልን በማለት ለፌደሬሽን ምክር ቤት ጥያቄ አቀረቡ። ይህ ከመሆኑ በፊት ግን መንግስት በራሱ አብደራፊንና መተማን ክፍለ ከተማ በማለት ሰይሟቸው ነበር። ክፍለከተማ ማለት የክልሉ መንግስት የማያዝበት ከተማ ማለት ነው። ይህ ሆን ተብሎ የተሰራ የቅድመ ዝግጅት ተንኮል ነው።

በአካባቢው የሚኖረው የአርማጭሆ ህዝብም ለምን እንዲህ አይነት ጥያቄ መጥየቅ አስፈለጋችሁ ብሎ ለትግራይ ሰፋሪዎች ሲጠይቃቸው አስተዳደሩ አልተመቸነም ሲሉ ትግሬዎቹ መልስ ሰጡ። የአርማጭሆ ህዝብም እኛ እየኖረነበት ያለው አስተዳደር ካልተመቻችሁና እንደኛ ሁናችሁ መኖር ካልቻላችሁ ተመልሳችሁ ወደ መጣችሁበት ወደ አገራችሁ ልትሄዱ ትችላላችሁ እንጅ አገራችን ልትወስዱ አትችሉም አላቸው። የተንኮላቸው ተንኮል ይህነን ጥያቄ ከመጠየቃቸው በፊት የአብደራፊን መዘጋጃ ቤት ባልታወቀ

*ሁኔታ በሳት ኢቃጥለው ይባስ ብለው ደግሞ ያርማጭሆ ተወላጆችን ያቃጠላችሁት እናንተ ናችሁ በማለት ይዘው አሰሯቸው። ይህ የተቃጠለ መዘጋጃ ቤት የብዙ ገበሬዎችን ስም ዝርዝር የያዘ ብዙ መዝገቦችንና ሰነዶችን የያዘ መስሪያ ቤት ነበር። ይህም ሆን ተብሎ ታሪካዊ መዝገቦችንና ሰነዶችን ለማጥፋት ተብሎ የተደረገ ተንኮል ነው።ነገሩ በዚህ አላበቃም ብዙም ሳይቆይ የትግራይ የክልል መንግስት መንገድ እየጠረገ ወደ አማራው ክልል ወደ አብደራፊና አካባቢው በቧሂትና ግጨው ቀበሌዎች መጡ።*

*በአርማችሆ እና በአካባቢው የሚኖረው ህዝብ የትነው የምትመጡት አቁሙ አላቸው።ትግሬዎቹም እኛ የመጣነው መንግድ ልንጠርግላችሁ ነው ሲሉ የተለመደ ማጭበርበራቸውን ጀመሩ የአርማጭሆ ህዝብም የኛን መንገድ የክልላችን መንግስት ይሰራል እንጅ እናንተን አይመለከታችሁም በማለት አስቆማቸው። በዚህ የተነሳ ከፍተኛ ረብሻ ተነስቶ ሁለቱ የክልል መሪዎች ጣልቃ እስከመግባት ተደርሶ ነበር።*

*የሚገርመው ነገር በዚህ ጊዜ የጸገዴንና የወልቃይትን የአካባቢ ሚሊሻ በአርማችሆ ህዝብ ላይ ዝመቱ ብለው አዘው ነበር። ሁለቱን ህዝቦች ለማጋጨትና ለማጋደል። ነገርግን የወልቃይትና የጸገዴ ሚሊሻዎች በወንድሞቻችን ላይ አንዘምትም ሲሉ ለወያኔ መሪዎች መለሱላቸው።በመልሱ የተናደዱ ወያኔውችም ይህነን ካላችሁ ያስታጠቅናችሁን መሳሪያ አውርዱ አሏቸው። ምልሻዎችም ውሰዱት በማለት አስረከባቸው። ከዛ በኃላ ወያኔዎች መደበኛውን የትግራይ ሰራዊት የደንብ ልብሱን አስወልቀው ተራ ባላገር በማስመሰል ባርማጭሆ ሕዝብ ላይ ለማዝመት ሞክረው ነበር።*

*በጣም የሚያሳዝነው ተንኮላቸው በዚህ ወቅት የቅማንትን ህዝብ በማነሳሳት በማንነት ጥያቄ ምክንያት ከወንድሙ ካማራ ህዝብ ጋር በማጋጨት የአካባቢውን ህዝብ ለመከፋፈል የሞከሩበት ጊዜ ነበር። በዚህ ጊዜ የወያኔን ሴራና የመሬት ዘረፋውን እንቅስቃሴ ለመመከት ተዋናኝ ከነበሩት የአርማጭሆና የአካባቢው ተወላጆች መካከል ብዙዎችን በተናጠል እየለቀሙ ወደ አልታወቀ እስር ቤት ወስደዋቸዋል። አሁንም ድረስ እስረኞቹ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኑ የታወቀ ነገር የለም። ለምሳሌ ከታሰሩት እስረኞች መካከል ጥቂቶችን በስም ለመጥቀስ ያክል፥ አቶ አዋጁ አቡሃይ አቶ ማሞ ሃይሌ  አቶ አንጋው እና የመሳሰሉት ይገኙበታል። ይህም የግፍ ድርጊት በወልቃይት ስበብ ለተቀጣጠለው የህዝብ አመጽ ዋና መቀጣጠያ ቤንዚን ሊሆን ችሏል።*

*ይቀጥላል*

*ከአትርሳው ተሰፋየ*

*11/2016*